actionaid

# ሥራ የሌላት ሴት የለችም!



**እውቅና እንስጥ　　ጫናውን እንቀንስ　　ሥራውን እንካፈል**

## የማይከፈልባቸው የቤት ውስጥ ሥራዎች እና ክብካቤዎች

ሴቶች ባሉበት ሁሉ ክብካቤ አገልግሎቶች ይገኛሉ – ልጆችዋን ከምትንከባከበው እናት ጀምሮ የቤተሰብዋን ምግብ እስከምታበስለው ሚስት፤ ወይ ደግሞ የቤት ውስጥ ሥራዎች ላይ የምትጠመደው የቤተሰቡ ሴት ልጅ ፤ አለፍ ሲልም ለዕድርተኞች ምግብ ለማሰናዳት ማድቤት ጉድጉድ የምትል ሴት... እነዚህ ከብዙ ጥቂቶቹ ለሴቶች የተተዉ የማይከፈልባቸው የቤት ውስጥ ሥራዎች እና ክብካቤ አገልግሎቶች ናቸው።

actionaid

## የማይከፈልበት የቤት ውስጥ ሥራ እና ክብካቤ ትርጉም

**'የማይከፈልበት'** የሚለው ቃል፥ ሥራው ወይም የክብካቤ አገልግሎቱ፥ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በግሉ ዘርፍ ክፍያ የማይፈፀምላቸው የሥራ አይነቶች መሆናቸውን ያመላክታለ

**'ክብካቤ'** የሚለው ቃል፥ አገልግሎቱ ሌሎች ሰዎችን የሚታደግ መሆኑን ያመለክታል።
***'ሥራ'*** የሚለው ቃል፥ ድርጊቶቹ ከሚወስዱት ጊዜ እና ከሚጠይቁት ጉልበት አንፃር ዋጋ ያላቸው እና ውል እንደሚገባላቸው የኮንትራት ወይም ማኅበራዊ ግዴታዎች የሚቆጠር መሆኑን ይጠቁማል።

መሰረታዊ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች በሌሉበት የማይከፈልበት የቤት ውስጥ ሥራ እና ክብካቤን መከወን ይበልጥ አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም ክብካቤውን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶችን ለመግዛት  የሚያስፈልግ ገቢ ላይኖር ይችላል። ይህ ሲሆን የሚያስፈልገውን የቤት ውስጥ ሥራ እና ክብካቤ ለመስጠት ሴቶች የራሳቸውን ጉልበት እና ጊዜ ይጠቀማሉ። ብዙዎቹ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች የቤት ውስጥ ሥራ እና ክብካቤን የማከናወን እና ለኑሮ መግፊያ የሚያስፈልጉ ወጭዎችን የመሸፈን ድርብ ሃላፊነት ይሸከማሉ። ሴቶች እነዚህን ሥራዎች እና ክብካቤዎች ለመስጠት በተጣለባቸው ሃላፊነት ምክንያት፥ ትምህርት የመማር፣ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ፣ ምቹ የሥራ እና የመዝናናት መብቶቻቸውን አጥተዋል። ይህም የተዛባ ሥርዓተ-ፆታ እንዲሰፍን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው።

## ምን ማድረግ እንችላለን?

ሦስት ዋና ዋና ርምጃዎችን መውሰድ እንችላለን፡-

- ***ለሥራው እውቅና መስጠት፡-*** በዋናነት በሴቶች የሚሰሩትን ሥራዎች ማየት እና እውቅና መስጠት። ይህም ድርጊቱን እንደ "ሥራ" ወይም እንደ "ምርት" መቁጠር ማለት ነው።
- ***ሥራውን መቀነስ፡-*** ሴቶች ላይ የተጫነውን የቤት ውስጥ ሥራ እና ክብካቤ አገልግሎት መቀነስ ያስፈልጋል። ይኸውም ሥራው ወይም አገልግሎቱ በተለየ ሁኔታ እንዲከናወን በማድረግ ሥራውን ማቃለል ይቻላል። ለምሳሌ፥ የህጻናት ክብካቤ መስጫ ማዕከል በተመጣጣኝ ዋጋ እና በቅርብ እንዲኖር በማድረግ እና ጊዜ እና ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን በማቅረብ፥ ሴቶች ላይ  ያለውን ጫና መቀነስ ይቻላል።
- ***ሥራውን ማከፋፈል፡-***  የሥራው መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራውን ግን በቤተሰቡ ውስጥ ለሚገኙ ወንዶች በማከፋፈል ሴቶች ላይ ያለውን ተደራራቢ ጫና እና ሃላፊነት መቀነስ

**ከሥራዎች ሁሉ ውድ፣ ክፍያ የማይፈፀምላቸው የቤት ውስጥ ስራዎች እና እንክብካቤዎች ናቸው!**